በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት
መስተዳደር ምክር ቤት
Benishangul Gumuz Regional State
ADMINISTRATIVE COUNCIL

ቁጥር/Ref.No. 332/ከ3/2 ...
ቀን/Date 22/04 /2016ዓ/ም

ለወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ማረጋገጫ ኤጀንሲ
አሶሳ

ጉዳዩ፡- የፀደቀ ደንብ ስለመላክ ይሆናል

የክልሉ መንግሥት መስተዳድር ም/ቤት (ካቢኔ) ታህሣሥ 02 ቀን 2016 ዓ/ም ባካሄደዉ አስቸኳይ ስብሰባዉ የክልሉ ነዋሪዎች መታወቂያ ይዘትና አሰጣጥን ለመወሰን በቀረበዉ ረቂቅ ደንብ ላይ ካቢኔዉ በስፋት ተወያይቶበት ማሻሻያዎችን በማከል ወደ ሥራ እንዲገባ ያፀደቀ ሲሆን ሥራዉም በኤጀንሲዉ በኩል ካሉት የተለያዩ መረጃዎችን አስደግፎ ለማከናወንና በተፈለገዉ መልኩ ሊሠራ እንደሚችል በማመን ከክልሉ ገቢዎች ባለሥልጣን ጋር አስፈላጊዉን የማሽንና የመረጃ ልዉዉጥ በማድረግ ሥራዉ በጥንቃቄ እንዲከናወን ጭምር ወስኗል፡፡

ስለዚህ ደንቡ ወደ ክልሉ መንግሥት ም/ቤት ጽ/ቤት ተልኮ የደንብ ቁጥር እንዲሰጠዉ ተደርጎ ደንቡ ቁጥር 266/2016 ተብሎ የደንብ ቁጥር የተሰጠዉ በመሆኑ በደንቡ አግባብ ህትመቱን ለማከናወን እንዲቻል በከተማዉ ህጋዊ ከሆኑ የህትመት ድርጅቶች ጋር ዉል በማግባት በጥንቃቄና ምሥጢሩን በጠበቀ መልኩ ሥራዉ እንዲከናወን እያሳሰብኩ፤የክልሉ ገቢዎች ባለሥልጣንም ይህንኑ አዉቆ ለሥራዉ መሳካት ኤጀንሲዉ የሚፈልገዉን የማሽን እገዛና ድጋፍ በማድረግ ሥራዉ ዉጤታማ እንዲሆን የበኩሉን ኃላፊነት እንዲወጣ ከአደራ ጭምር እያሳሰብኩ፣ለአፈፃፀም ያመቹ ዘንድ የደንቡ ሀርድ ኮፒ አንድ ጥራዝ ከዚህ ሸኚ ጋር በአባሪነት መላኩን አስታዉቃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

አሻድሊ ሀሰን አለአ...
ርዕሰ መስተዳደር

እንዲያውቁት

- ለክቡር ም/ርዕሰ-መስተደድር
- ለርዕሰ-መስተዳድርና ካቢኔ ጉ/ጽ/ቤት
- ለአቅም ግንባታና ማህበራዊ ዘርፍ አማካሪ
- ለአጀንዳ ውሣኔ ዝ/ሥ/ክ/ዳይሬክቶሬት
  በጽ/ቤቱ፣

ግልባጭ

- ለፋይናንስ ቢሮ
- ለፍትህ ቢሮ
- ለገቢዎች ባለሥልጣን
  አሶሳ፣

ስልክ/Tel 057-7750-218
ፋክስ/FAX 057-775-08-41/08-38
ፖሣቁ/P.O.Box 44

ቤኒሻንጉል - አዲሲቷ የተስፋ አድማስ
Benishangul - A New Horizon of Hope
Email : BGRSAC@gmil.com

ደንብ ቁጥር 166/2016 ዓ.ም

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ነዋሪዎችን መታወቂያ ይዘትና የአሰጣጥ ሂደትን ለመወሰን የወጣው ደንብ

የክልሉ ነዋሪ የተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶችን ማግኘት እንዲችል ለማድረግ እና ተደራሽ ቀልጣፋና ውጤታማ የመታወቂያ አሰጣጥ ሥርዓትን መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የክልሉን ነዋሪ ደህንነትን ለመጠበቅ እና በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ ለዜጎች የሚሰጡ አገልግሎቶችን ቀልጣፋ ለማድረግ እንዲያስችል ነባሩን መታወቂያ በዲጂታል መታወቂያ በመቀየር አስፈላጊ በመሆኑ፤

በተሻሻለዉ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት አንቀጽ 59 (1) መሰረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

   ይህ ደንብ "የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ነዋሪዎችን የመታወቂያ ይዘትንና አሰጣጥን ለመወሰን የወጣው ደንብ ቁጥር.160...../2016 ዓ/ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ፤

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

   1. "ክልል" ማለት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ማለት ነው፤
   2. "ነዋሪ" ማለት በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ዉስጥ በግል ወይም በመንግስት ስራ ላይ ተሰማርቶ በግሉ ወይም በመንግስት ወይም በግለሰብ ቤት ተከራይቶ፣ የሚኖር መደበኛ የመኖሪያ አድራሻ ያለው ስለመሆኑ በወረዳዉ ወይም በቀበሌ አስተዳደሩ የተመዘገበ ግለሰብ ማለት ነው፤
   3. "መደበኛ አድራሻ" ማለት ነዋሪዉ በክልሉ ውስጥ በግል መኖሪያ ቤት ወይም መንግስት በሚያከራቸዉ ቤቶች ወይም በግለሰብ ቤት በኪራይ ወይም ከቤተሰብ ጋር የሚኖርበት ወይም ከባለቤቱ ጋር ተጠግቶ ያለ ግለሰብ የሚኖርበት የመኖሪያ ቤት ያለበት አካባቢ ማለት ነው፤
   4. "የነዋሪዎች ምዝገባ" ማለት የነዋሪዎችን መረጃ በተሟላ መልኩ መዝግቦና አደራጅቶ የመያዝ ሂደት ነው፤
   5. "የአካባቢ መለያ ቁጥር" ማለት አንድ የክልሉ ነዋሪ ለሚኖርበት አካባቢ የተሰጠ የአካባቢ መለያ ቁጥር ማለት ነው፤
   6. "የግል መለያ ቁጥር" ማለት አንድ የክልሉ ነዋሪ በሚኖርበት የአከባቢ መለያ መነሻነት ተመዝግቦ በግል ማህደሩና በመታወቂያ ላይ የሚፃፍ ምስጢራዊ ቁጥር ነው፤
   7. "የቤተሰብ ተጠሪ" ማለት ባል ወይም ሚስት ወይም በህግ ወይም ሌላ በውክልና ወይም በህግ ቤተሰቡን እንዲያስተዳደር ኃላፊነት የተሰጠዉ ሰዉ ማለት ነው፤
   8. "የነዋሪነት መታወቂያ ካርድ" ማለት በክልሉ ውስጥ መደበኛ የመኖሪያ አድራሻ ላለዉና በመኖሪያ አካባቢው ተለይቶ በተሰጠ መለያ ቁጥር ለአንድ የክልሉ ነዋሪ የሚሰጥ የነዋሪነት ማረጋገጫ ካርድ ማለት ነው፤

9. "ካምፕ" ማለት የሀገር መከላከያ ሰራዊት አባላት፣ የፌደራልና የክልል ፖሊስ አባላት፣ ስደተኞችና ተፈናቃይ ዜጎች በጋራ የሚኖሩበት መኖሪያ ቤቶችን ወይም ክፍሎችን ወይም ሌሎች መጠለያዎችን የያዘ ግቢ ነው፤

10."ጊዜያዊ መጠለያ" ማለት ለተወሰነ የልማትና ማህበራዊ አገልግሎት ተብሎ ለተወሰነ ወይም ሳልተወሰነ ጊዜ የተገነባ የጎዳና ተዳዳሪዎች ለተሀድሶና ስልጠና የሚቆዩበት ማዕከል፣ የስራ ዕድል የተፈጠረላቸው ዜጎች የክህሎት ስልጠና እስኪጨርሱ የቆዩበት ማዕከላትና የመልሶ ማልማት ተነሺዎች የሚቆዩበት ጊዜያዊ ቤቶች ናቸው፤

11. "ጥገኛ" ማለት የራሱ መደበኛ ቦታ የሌለው ነገር ግን በነዋሪነት ከተመዘገበው ሰው ጋር ተጠግቶ የሚኖርና በዚህ ሰው መደበኛ መኖሪያ ቦታ ወይም አድራሻ የሚታወቅ ግለሰብ ነው፤

12. "አሰሪ" ማለት አንድን ሰው በቋሚነት ወይም በጊዜያዊ የአሰሪና ሰራተኛ ውል ገብቶ የሚያሰራ ሰው ነው፤

13. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም ህጋዊ ሰውነት የተሰጠው አካል ነው፤

14. በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ፆታ ያካትታል።

3. የተፈፃሚነት ወሰን፤

ይህ ደንብ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የነዋሪነት መታወቂያ ካርድ ባገኙ ሁሉም አካላት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

ክፍል ሁለት

ስለ ነዋሪነት መታወቂያ

4. የነዋሪነት መታወቂያ ለመዉሰድ የሚያበቁ መስፈርቶች

1. በአመልካች ተሞልቶ የተፈረመ ቅጽ፤
2. ማንኛዉም መታወቂያ ፈላጊ ቅድሚያ በመደበኛነት ከሚኖርበት ቀበሌ ወይም እንደ አስፈላጊነቱ በአካባቢዉ በሚገኝ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ጽህፈት ቤት የተመዘገበና ለነዋሪዎች ምዝገባ አገልግሎት ተብሎ በተዘጋጀ ቅፅ የተመዘገበ መሆን፤
3. ዕድሜያቸዉ 18 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆኑ ልጆች አባት ወይም እናት ወይም በህግ የማስተዳደር ወይም የመጠበቅ ስልጣን ያገኘ የቤተሰብ ተጠሪ ወይም ህጋዊ ውክልና የተሰጣቸው ተወካዮች በተወከሉበት ቤት እንደ ባለቤቱ ሆነው የሚያስተዳሩትን ሰዉ

በነዋሪዎች ቅፅ ላይ እንዲመዘገቡ ካደረጉ ተመዝጋቢዉ የነዋሪነት መታወቂያ ሊያገኝ ይችላል፡፡

4. ማንኛውም የክልሉ ነዋሪ የሚከተሉትን መረጃዎች ያሟላ መሆን አለበት፡-

ሀ. ሙሉ ስም ከነ አያት፣

ለ. የእናት ሙሉ ስም፤

ሐ. የትውልድ ቀን፣ ወር፣ ዓመተ ምህረት፣

መ. የትውልድ ቦታ፣

ሠ. መደበኛ የመኖሪያ ቦታ፣/ወረዳ፣ቀበሌ

ረ. ለምዝገባ ሲመጣ መጠኑ 2በ2 የሆነ ጉርድ ፎቶ ግራፍ፣

ሰ. የጋብቻ ሁኔታ፣

ሸ. የስራ ሁኔታ

ቀ. ዕድሜዉ 18 ዓመት የሞላዉ፤

5. ከሌላ አካባቢ የመጣ ከሆነ ከላይ በንዑስ አንቀፅ 4 ከተገለጸው መረጃ በተጨማሪ ቀድሞ ከሚኖርበት አካባቢ የተሰጠው መሸኛ ደብዳቤ በማቅረብ በነዋሪነት የተመዘገበ መሆን አለበት፤መሸኛውም የሚከተሉትን መረጃዎች ማሟላት አለበት፡-

ሀ. ሙሉ ስም ከነ አያት፣

ለ. የእናት ሙሉ ስም፣

ሐ. የጋብቻ ሁኔታ፣ ያገባ ከሆነና ልጆች ካሉት የባለቤቱ ስም ከነ ልጆቹ ፣ እንዲሁም ሌሎች አብረውት የተሸኙ የቤተሰቡ አባላት ስም ዝርዝርና እድሜያቸዉ ከ18 ዓመት በላይ የሆነ የቤተሰብ አባል ካለ በፎቶ ግራፍ የተደገፈ ሆኖ ፎቶ ግራፍ ከ3 ወር ወዲህ የተነሱ መሆን ይኖርበታል፤

መ. የትውልድ ቀን፣ ወር ፣ ዓመተ ምህረት፣

ሠ. የትውልድ ቦታ፣

ረ. የመሸኛው ቀንና ቁጥር፤

ሰ. መሸኛውን የሰጠው ህጋዊ አካል ወይም ባለስልጣን ወይም ባለሙያ ሙሉ ስምና የኃላፊነት፤የተቋሙ የራስጌና ግርጌ ማህተም ያረፈበት መሆን አለበት፤

ሸ. መሸኛው ላይ የለቀቀበት ምክንያት መገለፅ አለበት፣

ቀ. ይኖር የነበረበትን አድራሻ ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ቀበሌ፣ የቤት ቁጥር

በ. መሸኛው ላይ ያልተሟሉ ነገሮች ካሉ ሌሎች ህጋዊ መረጃዎች በማቅረብ እና እንደ አስፈላጊነቱ በቃለ-መሀላ መረጋገጥ አለበት፤

6. የነዋሪነት መታወቂያ ይዘት

1. የነዋሪነት ድጅታል መታወቂያ በጥንቃቄና ምስጥራዊነቱን ጠብቆ የሚታተም ሆኖ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፡-

ሀ. ስም ከነ አያት፤

ለ. የእናት ሙሉ ስም፤

ሐ. የትውልድ ዘመን /ቀን፣ ወር ፣ ዓመተ ምህረት፣

መ. ፆታ፣ዜግነት፣የስራ ሁኔታ፣

ሠ. መደበኛ የመኖሪያ አድራሻ፡- ወረዳ፣ ቀበሌ፣ የቤት ቁጥር፣

ረ. የግል መለያ ቁጥር፣የቤተሰብ ፋይል ቁጥር

ሰ. በአደጋ ጊዜ የቅርብ ተጠሪ ስም አድራሻ፣ የመስሪያ ቤት ወይም የመኖሪያ ቤት ስልክ ቁጥር ወይም የሞባይል ስልክ ፤

ሸ. ባር ኮድ፤

ቀ. ሎጎ

ተ. መታወቂያ የተሰጠበት ቀን፣ወር፣ ዓመተ ምህረት እና የአገልግሎት ዘመኑና አገልግሎት የሚያበቃበት ቀን፣

ቸ. መታወቂያ የሰጠው ኃላፊ ስምና ፊርማ፤

2. የነዋሪነት መታወቂያ ጠያቂዎችን ዝርዝር የያዘ ዋና ሰነድ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ስር ከተዘረዘሩት በተጨማሪ ዝርዝር ሁኔታዎች መያዝ አለበት፡፡

ሀ. ተራ ቁጥር ፣ቅፁንና የተመዘገበበትን ጥራዝ፤

ለ. በአከባቢ መለያ ቁጥር መነሻነት የሚሰጥ መለያ ቁጥር መያዝ አለበት፡፡

ሐ. የቤተሰብ ፋይል ቁጥር

3. የነዋሪነት መታወቂያ በየሁለት ዓመት የሚታደስ ይሆናል፡፡

7. የነዋሪነት መታወቂያ አሰጣጥ ሂደት

1. በሚኖርበት ቀበሌ ወይም ወሳኝ ኩነት ጽህፈት ቤቶች በነዋሪዎች ምዝገባ ቅጽ ላይ የተመዘገበ ሰው የነዋሪነት መታወቂያ እንዲሰጠው የመጠየቅ መብት አለው፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ጥያቄ የሚያቀርብ አመልካች በሚኖርበት ቀበሌ ጽ/ቤት በአካል ቀርቦ ከ 6 ወር ወዲህ የተነሳውን 2 ጉርድ ፎቶግራፍ በመያዝና የተዘጋጀውን ቅጽ መሙላት ይጠበቅበታል፡፡
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት የተደረገ ምዝገባ በቀበሌዉ በኩል ለወረዳ፣ለከተማ አስተዳደር ወይም ማዘጋጃ ቤት ዝርዝሩ ይቀርባል፡፡
4. እያንዳንዱ የቀረበ የመታወቂያ ፈላጊ ዝርዝር በቀበሌዉ በኩል ተሞልቶ ከተላከ በኂላ ግለሸቡ በትክክል የቀበሌዉ ነዋሪ ስለመሆኑ በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳሩ በኩል ለቀበሌዉ ነዋሪ እንዲቀርብ በማድረግ ነዋሪ መሆናቸዉ ከተረጋገጠ በኂላ ህትመቱ እንዲፈፀም ይደረግና እንደየ አካባቢ የወረዳ፣የከተማ አስተዳደር ወይም የከተማ አስተዳደሩ ማህተም ካረፈበት በኂላ ለቀበሌዉ ይመልሰዋል፣ ስርጭቱም በቀበሌዉ በኩል ይፈፀማል፡፡
5. መታወቂያ በውክልና አይሰጥም፡፡
6. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4 የተመለከተዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለመታወቂዉ ቀደም ሲል አስፈላጊዉን መስፈርት አሟልቶ ከሆነ በልዩ ሁኔታ ተወካይ የሆነ ሰዉ ሊወስድለት ይችላል፣
7. በሚኖርበት ቀበሌ በነዋሪዎች ምዝገባ ቅጽ ላይ የተመዘገበ ሰው ማንኛዉም በሰራተኛነት ቀጥሮ የሚያስተዳራቸውን ግለሰቦች መታወቂያ እንዲያገኙ አስፈላጊዉን ሁሉ ያደርጋል፡፡
8. በውጭ ሀገር ሲኖር የነበረ ኢትዮጵያዊ ዜግነቱን ለመቀየሩንና በነዋሪነት የተመዘገበና በነዋሪነት በከተማው ዉስጥ መኖሩ ከተረጋገጠ የነዋሪነት የመታወቂያ ሊሰጠው ይችላል፡፡
9. የነዋሪነት መታወቂያ የሚጠይቅ ማንኛውም ግለሰብ በክልሉ ውስጥ መደኛ ነዋሪ የሆነና የግል መኖሪያ ቤት ያለው ከሆነ የቤት ባለቤትነት የሚያረጋግጥ ሰነድ፣ በመንግስት ኪራይ ቤቶች ዉስጥ የሚኖር ወይም ተከራይ ከሆነ ደግሞ ይህንን ለመመዝገብ ስልጣን ባለዉ አካል ፊት የተመዘገበ የተከራይ አከራይ ዉልና ከሌላ ቦታ ከመጣ ሸኚ ደብዳቤዉን በማቅረብ የነዋሪነት መታወቂያውን ሊያገኝ ይችላል፡፡
10. በመንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ዉስጥ የሚሰሩ መምህራንና ሰራተኞች በተቋማቱ በተገነቡ የመኖሪያ ቤቶች ዉስጥ የሚኖሩና መታወቂያ ማግኘት የሚፈልጉ ከሆነ ከየተቋማቱ በሚሰጥ ማረጋገጫ አግባብ እየታዩ አገልግሎቱን ሊያገኙ ይችላል፡

8. የነዋሪነት መታወቂያን ስለማደስና ምትክ ስለመስጠት

1. በዚህ ደንብ መሠረት የነዋሪነት መታወቂያ የተሰጠው ነዋሪ የአገልግሎት ዘመን ሲያበቃ ቀደም ሲል የተሰጠዉ መታወቂያው ተመላሽ ተደርጎ አዲስ ይሰጠዋል፡፡
2. የተሰጠው መታወቂያ የተቀደደበት ወይም የተቃጠለበት ወይም የተበላሸበት ወይም በሌላ በማኛውም ምክንያት አገልግሎት መስጠት በማችልበት ደረጃ የደረሰበት ነዋሪ ወዲያውኑ ለሰጠው አካል በጹሁፍ ሲያመለክት እና ቃለ-መሀላን ጨምሮ ተጨባጭ ማስረጃ ሲያቀርብ በአንቀፅ 10 ንዑስ አንቀፅ 1(ለ) መሰረት ክፍያ ፈፅሞ ምትክ መታውቂያ ይሰጠዋል፡፡
3. መታወቂያ የጠፋበት ነዋሪ ስለመጥፋቱ ከአካባቢው ፖሊስ ጽህፈት ቤትና ከቀበሌዉ ማህበራዊ ፍርድ ቤት የጠፋበት ስለመሆኑ ማስረጃ ካመጣና አመልካች በነዋሪነት ቅጽ ላይ መመዝገቡ ከተረጋጠ እንደአስፈላጊነቱ በቃለ-መሀላ እንዲያረጋግጥ በማድረግ በአንቀፅ 10 ንዑስ አንቀፅ 1(ለ) መሰረት ክፍያ ፈፅሞ በምትኩ ይሰጠዋል፡፡

9. መታወቂያ ለማሳደስ የሚቀርብ ጥያቄ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን መያዝ ይኖርበታል፤

ሀ. እንደ አስፈላጊነቱ ከ3 ወር ወዲህ የተነሳ 2 ፓስፖርት ሳይዝ ፎቶ ግራፍ፤

ለ. ከሚኖርበት ቀበሌ ወይም ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ጽህፈት ቤት የታደሰ የነዋሪነት መረጃ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡

ሐ. የባለ መታወቂያዉ መረጃ ላይ ለዉጥ ካለ እንደ አዲስ ይመዘገባል፤

መ. የእድሳት ጥያቄዉ የቀረበዉ በተወካይ ከሆነ ተወካይ ከዉክልና ማስረጃዉ ጋር የራሱን መታወቂያ ኮፒ አድርጎ በማቅረብ ተገቢዉን ክፍያ ከፈፀመ ሊታደስ ይችላል፡፡

10. የአገልግሎት ክፍያ ሁኔታ፤

1. ማንኛዉም መታወቂያ ለመዉሰድ ያመለከተና ቀደም ሲል ወስዶ የነበረ ነዋሪ ከዚህ በታች በተገለፀዉ ልክ ክፍይ በመፈፀም መታወቂያ እንዲያገኝ ይደረጋል፤

ሀ. አዲስ የመታወቂያ ወረቀት ለመዉሰድ ....ብር 350.00

ለ. ለመቀዬር/ትክ ለመዉሰድ...ብር 350.00

ሐ. ለዕድሳት ....ብር 300.00

መ. በባለ መታወቂያዉ ስህተት ለመጣ ግድፈት ....ብር 350.00

2. በተቀመጠዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ ያልቀዬረ ነዋሪ ቀጥሎ በተገለፀዉ አግባብ ክፍያ በመፈፀም አገልግሎቱን እንዲያገኝ ይደረጋል፡

ሀ. ለመጀመሪያ አንድ ወር ብር 375.00 ክፍያ መፈፀም የሚጠበቅበት ሆኖ በዚህ ጊዜ ዉስጥም ካልቀዩረ ከሁለተኛዉ ወር ጀምሮ ባሉት ጊዜያት ባልታደሰባቸዉ ጊዜያት ልክ በብር 375.00 ሳያሳድስ የቆየባቸዉ ወራቶች ብዛት በ75 እየተባዛ ክፍያ እንዲፈፅም በማድረግ መታወቂያ ማግኘት ይችላል፡፡

ለ. እድሳቱ የዘገዩዉ ከአቅም በላይ ከሆነ ይኸዉ ሁኔታ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት መሆኑ ከተረጋገጠ ብር 300.00 ከፍሎ መዉሰድ ይችላል፡፡

ሐ. ቀደም ሲል ይኖርበት የነበረን አካባቢ በሙተዉ ወደ ሌላ አካባቢ የመኖሪያ አድራሻ የሚቀይር ከሆነ በዚህ አድራሻ የወሰደዉን መታወቂያ ለአካባቢዉ በመመለስ በአዲሱ አድራሻ ብር 150.00 በመክፈል አካባቢ በመመለስ በምትኩ አዲስ መታወቂያ ይሰጠዋል፡፡

መ. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 ስር የተዘረዘሩት የክፍያ ሁኔታዎች ቢኖሩም የመክፈል አቅም ለሌላቸዉ የህብረተሰብ ክፍሎች ከሚኖሩበት ቀበሌ የተሰጠና በወረዳ በከተማ አስተዳደሮችና በማዘጋጃ ቤቶች በኩል የተረጋገጠ ማስረጃ ሲቀርብ ተጣርቶ ክፍያቸዉ በወረዳ በከተማ አስተዳደሮችና በማዘጋጃ ቤቶች በኩል እየተሸፈነ አገልግሎቱን እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

11. ነባሩን መታወቂያ ስለመተካት፤

1. ማንኛዉም የክልሉ ነዋሪ ይህ ደንብ ከፀደቀበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት በአንድ ዓመት ጊዜ ዉስጥ ቀደም ሲል የወሰደዉን መታወቂያ በመመለስ አዲሱን መታወቂያ እንዲወስድ ይደረጋል፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተመለከተዉ እንደተጠበቀ ሆኖ በተገለጸዉ ጊዜ ዉስጥ ያልመለሰዉ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን ካስረዳ ይህ ከአቅም በላይ የሆነዉ ምክንያት ከተወገደ በኋላ ባለዉ ሶስት ወር ጊዜ ዉስጥ ነባሩን በመመለስ አዲሱን መታወቂያ መዉሰድ አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 መሰረት ባሉት የጊዜ ገደቦች ዉስጥ ነባሩን መታወቂያ በመመለስ አዲሱ መታወቂያ ያልወሰደ የክልሉ ነዋሪ በአንቀጽ 10(2) ፊደል ተራ ሀ ስር በተመለከተዉ ልክ ተገቢዉን ክፍያ ከፍሎ መታወቂያዉን ማግኘት ይችላል፡፡

12. መታወቂያ ለመዉሰድ ስለሚቀርብ ጥያቄ፤

1. ማንኛዉም የክልሉ ነዋሪ ተፈላጊዉን መስፈርት አሟላቶ ከቀረበ ጥያቄዉ በቀረበ (3) /ሶስት / የስራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ዉስጥ እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

2. አመልካቹ አስቸኳይ ሁኔታ ከገጠመዉና የጥያቄዉ አግባብነት ካታመነበት መታወቂያዉን ያለ ወረፋ እንዲሰጠዉ ሊደርግ ይችላል፤

3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ አመልካቹ ቀደም ሲል መታወቂያ ለማግኘት ያላመለከተ ከሆነ ጥያቄዉ ለቀበሌዉ ቀርቦ ቀበሌዉም የጥያቄዉን ትክክለኛነት በማጣራት ለወረዳዉ በመላክ አገልግሎቱን እንዲያገኝ ይደረጋል።

ክፍል ሰስት

13. የክልሉ መንግስት ተግባርና ኃላፊነት

የክልሉ መንግስት ለመታወቂያ ህትመት የሚዉል የማሽነሪ ግዥ በመፈፀምና በዘርፉ የሰለጠነ የሰዉ ኃይል በማፍራ የህትመት ስራዉን በራሱ ማከናወን እስኪጀምር ድረስ የነዋሪዉን የመታወቂያ ችግር ለመቅረፍ ከልማት ድርጅቶች ወይም ህጋዊ ከሆነ የግል ድርጅቶች ጋር የተወሰነ ድርሻ በመያዝ የህትመት ስራዉን ማሰራት ይችላል፤

14. የክልሉ ወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ ተግባርና ኃላፊነት፤

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 13 ስር የተደነገገዉ እንደተጠቀበ ሆኖ የክልሉ ወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ የክልሉን መንግስት በመወከል በዘርፉ ከተሰማሩና ልምድ ካላቸዉ ድርጅቶች ጋር የክልሉን መንግስት ጥቅም ባስጠበቀ ሁኔታ በጋራ የመስራት ዉል ይዋዋላል፤ ስራዉን በበላይነት ይመራል፤ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል ለድርጅቱ ምቹ የስራ ቦታ ይፈጥራል፤
2. በዚህ ደንብ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀፅ 4 መሰረት እንያንዳንዱ መታወቂያ ከሚገኝ ክፍያ የመንግስት ድርሻ ገቢ በማድረግ ቀሪዉን ለድርጅቱ ይሰጣል፤
3. ለወረዳ፣ ለከተማ አስተዳደር ወይም ለማዘጋጃ ቤቶች ከህትመት ድርጅቱ ጋር የመታወቂያ ህትመት ዉል በመግባት እንዲታተምለት ያደርጋል።
4. የህትመት ስራዉ ሚስጥራዊነቱና ጥራቱን በጠበቀ ሁኔታ ስለመታተሙ ይቆጣጠራል፤
5. በህትመት ወቅት ህገ ወጥ ስራ ተሰርቷል ብሎ ሲያምን ወይም መረጃ ሲደርሰዉ ወይም በማናቸዉም ሌላ ምክንያት የህትመት ስራዉን የሚሰራዉን ድርጅት ስራ በራሱ ወይም በሌላ የዘርፉ ባለሙያ ማስመርመር ይችላል፤
6. የመታወቂያ ፈላጊዎች ዝርዝር በወረዳ፣ በከተማ አስተዳደር ወይም በማዘጋጃ ቤቶች በኩል እንዲደ ተጠቃሎ ለድርጅቱ መቅረቡን ይከታተላል፤
7. መታወቂዉ ለነዋሪዎች ምስጢራዊ በሆነ ሁኔታ መታተሙንና በአግባቡ መሰራጨቱን የመከታተል ሃላፊነት አለበት።

8. እንዲታተም ከታዘዘዉ ዉጭ ታትሞ ከተገኘ ለሚመለከተዉ የህግ አካል የማሳወቅ፣ እርምጃ እንዲወሰድ የማድረግ፣የተወሰዱ እርምጃዎችን የመከታተል፤

15. የወረዳ፣ የከተማ አስተዳደር፣ የማዘጋጃ ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት

1. መታወቂያ የወሰዱ ነዋሪዎችን ዝርዝር በአግባቡ አደራጅቶ የመያዝ፤
2. የእያንዳንዱን ተመዝጋቢ መረጃ በጥንቃቄ ያለ ስርዝ ድልዝና ስህተት የተመዘገበ መሆኑን የመከታተል፤
3. ለሚቀርቡ ቅሬታዎች ተገቢዉን ምላሽ የመስጠት ተግባርና ኃላፊነት አለባቸዉ፤

16. የነዋሪዉ መብትና ግዴታ

1. የተዘጋጀዉን ፎርም ሞልቶ የመፈረም፣
2. በመዝጋቢው አካል ፊት በአካል ቀርቦ ለዚሁ ተግባር በተዘጋጀ መዝገብ ላይ መመዝገብ፤
3. አስፈላጊዉን መስፈርት ካሟላ መታወቂያ የማግኘት
4. በተለያዩ ምክንያት መታወቂያ የወሰደበትን አካባቢ ለቆ የሚሄድ ነዋሪ ይህንኑ አሳዉቆ መታወቂያውን በመመለስ አለበት፤
5. ባለ መታወቂያው በክልሉ ዉስጥ ቀደም ሲል የነበረበትን አካባቢ ለቆ ወደ ሌላ የመኖሪያ አድራሻ የሚቀይር ከሆነ ይህንኑ የሚገልጽ ማስረጃ እንዲሰጠዉ የመጠየቅና አዲስ ለሚሄድበት ወረዳ ወይም ቀበሌ ይህንኑ ማስረጃ በማቅረብ ተገቢዉን ክፍያ በመፈፀም መታወቂያ ማግኘት መብት አለዉ፤
6. ከፍ ሲል በንዑስ አንቀፅ 4 የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ጥያቄዉ የቀረበለት የወረዳ መስተዳደር መረጃዉ ተሟልቶ እንዲላክለት ለቀበሌ ጽህፈት ቤት መመለስ አለበት፡
7. ማንኛውም ነዋሪ መታወቂያ ለመውሰድ ጥያቄ ሲያቀርብ ትክክለኛ የሆነ የቃልም ሆነ የሰነድ ማስረጃ የማቅረብ፤
8. መታወቂያዉን በጥንቃቄ የመያዝ ግዴታ አለበት፤

17. ስለ ቤት አከራይ

የቤት አከራይ የሆን ሰዉ ተከራዩ የግለሰቡን ቤት ተከራይቶ ቢያንስ 1/አንድ/ ዓመትና ከዚያ በላይ ከቆየና ቋሚ የመንግስት ሰራተኛ መሆኑን ከሚሰራበት መስሪያ ቤት ካረጋገጠ ተከራዩ የአከራዩን ቤት በመኖሪያ አድራሻነት በማስመዝገብ መታወቂያ እንዲያገኝ ሊያደርግ ይችላል።

ክፍል አራት

ስለ ቤተሰብ ተጠሪ፤ ለዉጥ ስለማድረግና ግድፈትን ስለማረም

18. ስለ ቤተሰብ ተጠሪ

ለመታወቂያ አሰጣጥ እንዲያገለግል በሚሞላዉ የምዝገባ ቅፅ ላይ የቤተሰብ ተጠሪ በሚለው ስፍራ፡-

1. በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ባልና ሚስት ያሉ ከሆነ በአንድነት የቤተሰቡ ተጠሪ ሆነው የሁለቱም ስምና ተገቢው መረጃ ይመዘገባል፤
2. ከባል ወይም ሚስት አንዱ ብቻ ያለ በሚሆንበት ጊዜ ያለው ሰው ተጠሪ ሆኖ በመጠይቁ መሠረት ስምና አስፈላጊ መረጃ ይመዘገባል፤
3. ሌላ ተጠሪ በሚለው ስፍራ ልጆች፣ የልጅ ልጆች፣ወንድም፤እህት ወይም ሌሎች ዘመዶች በሚመዘገቡበት ጊዜ የዝምድና ደረጃዉ ተገልፆ አግባብነት ባለው የነዋሪዎች ምዝገባ ቅፅ ላይ ይመዘገባል፤
4. አባትና እናት በህይወት ባለመኖራቸው ወይም በሌላ ህጋዊ ምክንያት ቤተሰብን እንዲያስተዳር በፍርድ ቤት የተሰየመ ሞግዚት ለቤተሰቡ ተጠሪ ይሆናል፤
5. ሌላ ቤተሰብ ሳይኖር ራሱን ችሎ ለብቻው የሚኖር ሰው የቤተሰቡ ተጠሪ ሆኖ ይመዘገባል።

19. ለዉጥ ስለማድረግና ግድፈትን ስለማረም

1. አንድ ሰው መታወቂያ ካገኘ በኋላ የስም ለውጥ አድርጎ መታወቂ ለመዉሰድ ጥያቄ ሲያቀርብ ጥያቄው ተቀባይነት የሚኖረዉ የስም ለዉጥ ስለመደረጉ በፍርድ ቤት ቀርቦ የተወሰነና የዉሳኔዉ ግልባጭ ከማመልከቻዉ ጋር ተያይዞ የቀረበ ከሆነ ይህንኑ እንደአስፈላጊነቱ በማረጋገጥ ብቻ ይፈጸማል።
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት የቀረበዉ ጥያቄ አስፈላጊዉ ማጣራት ተደርጎ ተቀባይነት ካገኘ የፍርድ ቤቱ የዉሳኔ ግልባጭ ቀደም ሲል ከተሞላዉ ቅፅ ጋር እንዲያያዝ ተደርጎ እንደ አዲስ ክፍያ በመፈፀም መታወቂያ መዉሰድ ይችላል፤

3. በመታወቂያ ወረቀት ላይ የፊደል ግድፈት ወይም ማንኛዉም የማስተካከል ጥያቄ ሲቀርብ ማስተካከያው ለአንድ ጊዜ ብቻ ሆኖ፡-

ሀ. ግድፈቱ የተከሰተው በየደረጃዉ ባለ የአገልግሎት ሰጪው ተቋም ባለሙያ መረጃዉ ሲሞላ በተፈጠረ ስህተት መሆኑ ሲረጋገጥ ያለምንም ክፍያ እዲስተካከል ወይም እንዲታረም ተደርጎ ወጪዉ ግድፈቱን በፈጠረዉ ባለሙያ የሚሸፈን ይሆናል፡፡

ለ. ግድፈቱ የተከሰተዉ በራሱ በባለመታወቂያዉ መረጃዉን ሲሞላ የተፈጠረ መሆኑ ከተረጋገጠ ተገቢዉን ክፍያ እንዲከፍል ተደርጎ እንዲታረም ይደረጋል፡፡

ክፍል አምስት
የተከለከሉ ተግባራት

20. መረጃ በሚሞሉ ባለሙያዎች የተከለከሉ ተግባራት

1. ባልተሟላና ትክክለኛነቱ ወይም ህጋዊነት ሳያረጋግጥ ምዝገባ ማካሄድ፤
2. በቀረበዉ የአመልካች የምዝገባ የጊዜ ቅደም ተከተል መሰረት ያለማስተናገድ፤
3. ሌሎች ህገ ወጥ ተግባራትን መፈፀም የተከለከለ ነዉ፤

21. የመታወቂያ ህትመት ስራ እንዲሰራ ከመንግስት ጋር የተስማማ ማንኛዉም አካል፤

1. በልዩ ሁኔታ በሚመለከተዉ አካል የተፈቀደ ካልሆነና ከህቅም በላይ ተብሎ በሚታሰብ ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር በተናጠል የሚቀርቡ የህትመት ጥያቄዎችን ተቀብሎ ማስተናገድ የተከለከለ ነዉ፤
2. ተገቢዉን መስፈርት ላላሟላ ግለሰብ መታወቂያ እንዲያገኝ እንዲያገኝ ማድረግ የተከለከለ ነዉ፤
3. የክልሉ/የአካባቢዉ/ ነዋሪ መሆኑን ሳያረጋግጥ መታወቂያ ማተም የለበትም፤
4. በምዝገባ ወቅትም ሆነ ከምዝገባ በኋላ መታወቂያ ሲሰጥ ወይም ከዚያ በኋላ በቅፆችም ሆነ በኮምፒዩተር ላይ ስለ ነዋሪው መረጃ አላግባብ ስርዝ ድልዝ ወይም ለውጥ ያለማድረግ፤
5. በህገ ወጥ መንገድ የታተመ መታወቂያ ስለመኖሩ ዉል ሰጪዉ አካል መረጃ ደርሶት እንዲጣራ ሲታዘዝ ተገቢዉን ትብብር ያለማድረግና
6. ሌሎች ህገ-ወጥ ተግባራትን መፈፀም የተከለከለ ነዉ፤

22. በነዋሪው የተከለከሉ ተግባራት፤

1. ማንኛውም ነዋሪ በክልሉ ዉስጥ ከአንድ በላይ የነዋሪነት መታወቂያ ካርድ ለመዉሰድ መመዝገብ፤
2. ሐሰተኛ መረጃ በማቅረብ የመታወቂያ ወረቀት መውሰድ፤
3. መታወቂያዉን ለሌላ አሳልፎ መስጠትና
4. መታወቂያዉ ለማንኛዉም ህጉ ወጥ ተግባር መጠቀም ፈፅሞ የተከለከለ ነዉ፤

23. ስለተጠያቂነት

1. በህትመት ስራ ላይ የሚሳተፍ ማንኛዉም አካል እንዲታተም ከታዘዘዉ ሌላ የነዋሪነት መታወቂያ አትሞ ቢገኝ በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል፡፡
2. ማንኛዉም የክልሉ ነዋሪ በህገ ወጥ መንገድ የታተመ ከአንድ በላይ የነዋሪነት መታወቂያ ይዞ የተገኘ እንደሆነ ህጋዊዉ መታወቂያ ጭምር ዋጋ እንዳይኖረዉ ተደርጎ አግባብነት ባላቸዉ ህጎች መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፤
3. በሐሰተኛ ሰነድ ወይም መረጃ የነዋሪነት መታወቂያ የወሰደ ግለሰብ የወሰደው መታወቂያ መሰረዙ እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብነት ባለዉ ህግ ተጠያቂ ይደረጋል፡፡
4. ይህ ድጅታል መታወቂያ በስራ ላይ ከዋለ በኂላና የመቀየሪያ ጊዜዉ ማለፉን እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባዉ ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት በነባሩ ወይም በተቀየረዉ መታወቂያ አገልግሎት መስጠትም ሆነ አገልግሎት መጠየቅ ለጉዳዩ አግባብነት ባላቸዉ ህጎች መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፤
5. በዚህ መመሪያ ላይ የተመለከቱ አጠቃላይ ክልከላዎችን ተላልፎ የተገኘ ማንኛዉም አካል እንደአስፈላጊነቱ በፍትሀብሄር እና አግባብነት ባላቸዉ የወንጀል ህጎች ተጠያቂ ይሆናል፡፡

ክፍል ስድስት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

24. ስለ ተፈፃሚነት፤

- ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ህግ ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

25.መመሪያውን ስለማሻሻል

የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይህን ደንብ ሊያሻሽለዉ ይችላል፡፡

26. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይህን ደንብ ለማስፈጸም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

27. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ፤

ደንቡ በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አሶሳ፤ ታኅሣሥ 2/2016 ዓ.ም

አሻድሊ ሀሰን አልአጀብ

ርዕሰ መስተዳደር